# እንቁራሪት



1ኛ ክፍል

29-30ኛው ሳምንት

መጽሐፍ 15

# እንቁራሪት

መጽሐፍ 15 | 1ኛ ክፍል | 29-30ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ።

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



ከዕለታት አንድ ቀን በሬና እንቁራሪት ተገናኙ።

በሬ ሳር ይግጣል።
እንቁራሪት ቆማ
ተመለከተችው። በበሬ
ትልቅነትና ውፍረት ቀናች።

በሬን በቁመትና በውፍረት ለመብለጥ አሰበች፡፡ ያሰበችውን ለማሳካት ዘዴ ቀየሰች፡፡ ዘዴዋንም ለጉዋደኛዋ አማከረቻት፡፡ ጉዋደኛዋም በሃሳቡዋ ተስማማች፡፡



እንቁራሪት ለማደግና ለመወፈር ብዙ መመገብ ጀመረች:: ትንንሽ ነፍሳትን ተመገበች:: በአጭር ጊዜ ውስጥ በጣም ወፈረች::



የህመም ስሜት ተሰማት::
አንድ ቀን በጣም አመማት::
ማቃሰት ጀመረች::
ህይወቱዋም አለፈ::

ጉዋደኛዋ ለቤተሰቦቿዋ
መርዶ ለመናገር ሄደች::
“ምን ሆና ሞተች?”
አሉዋት:: “በሬን አክል
ብላ ተተርትራ ሞተች”
ብላ አረዳቻቸው::

USAID

ከአሜሪካን ህዝብ